# በትራንስፖርት ሚኒስቴር

## የትራንስፖርት ባለሥልጣን

## የድንበር ተሻጋሪ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር የደረጃ አሰጣጥ መስፈርትና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የአፈፃፀም

## መመሪያ ቁ- 689/2013

ጥቅምት 2006 ዓ.ም

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ላይ ስትሆን፣ እየተመዘገበ ካለው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጐት በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ነው። እያደገ የመጣውን የትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጐት በአግባቡ በመመለስ የግብርና ምርቶችና የፋብሪካ ውጤቶች ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በሆነ አግባብ በማጓጓዝ ለተጠቃሚው የሚያደርሱ የትራንስፖርት ድርጅቶች፣ ኩባንያዎች፣ ማኀበራትና የግል ትራንስፖርተሮች አደረጃጀትና አሠራር በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በሰለጠነ የሰው ሀይል እንዲሁም በቂ የመረጃ ሥርዓት የተዘረጋለት ሆኖ አገልግሎት አሰጣጡ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ ሆኖ እንዲራመድ ማድረግ ያስፈልጋል፣

- የጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ በዉድድር ስርዓት ያልተጠናከረ በመሆኑ፤
- ዘርፉ በቅልጥፍናና በጥራት ተከታታይ እድገት የማይታይበት በመሆኑ፤
- የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎቱ ለደላላ የተጋለጠ በመሆኑ፤
- የአመለካከት ለውጥ የሚያመጣ አደረጃጀት ለመፍጠር፤
- ልማቱን በሚጠቅም ሁኔታ የዘርፉን ዓቅም ለማሳደግ፤
- የጭነት ትራንስፖርት በዋጋ ተዋዳዳሪ እዲሆን ለማስቻል፤

በተለይም ጭነት የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጡ የትራንስፖርት ድርጅቶች፣ /ኩባንያዎች፣/ ማኀበራትና የግል ትራንስፖርተሮች ከዘልማዳዊ አሰራር ተላቀው በአገልግሎታቸው ብቃትና ጥራት ተለይተው እንዲሠሩ በማድረግ በዘርፉ ያላቸውን ጉልህ ሚና በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ እንዲያከናውኑ ማድረግና፣ የአገሪቱ ምርቶች በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል አደረጃጀት ፈጥረው ሀገራዊ ሀላፊነታቸውን መውጣት ይኖርባቸዋል።በግልጽ የመለኪያ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተ የውድድር ሜዳ በመፍጠር ጤናማ የአገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ፣ አገልግሎት በመስጠት ላይ የተሠማሩ ትራንስፖርተሮች ውስጣዊ አሠራራቸውን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በማጠናከር የተሽከርካሪዎች ስምሪት በጠንካራ አደረጃጀትና ሰው ሀይል እየታገዘ በሥርዓት የሚመራበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ አስፈልጓል።

በመሆኑም ይህ የድንበር ተሻጋሪ የጭነት ትራንስፖርት ማኀበራትና ድርጅቶች አገልግሎት አሰጣጥ የደረጃ መሥፈርትና የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ኃ/ማርያም
ዳይሬክተር

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## 2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የድንበር ተሻጋሪ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር የደረጃ አሰጣጥ መሥፈርትና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የአፈፃፀም መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 3. **ትርጓሜ**

በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/97 እና በየብስ ዕቃን ስለማጓጓዝ በወጣው አዋጅ - 547/99 የተቀመጡት ትርጓሜዎች እንደአግባብነታቸው ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት አላቸው፣ በተጨማሪም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ

1. "**የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ**" ማለት ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ ወይም ጭነት እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራ ባለሞተር የጭነት ተሽከርካሪ ነው።
2. "**የብቃት ማረጋገጫ**" ማለት "በዚህ መሥፈርት መሠረት በጭነት ማመላለሻ ንግድ ሥራ ለተሠማሩ ማኅበራትና ድርጅት የሚሰጥ የደረጃ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ነው።
3. "**ደረጃ**"ማለት በጭነት ማመላለሻ ባለንብረቶች ማኅበርና ድርጅቶች ኦፕሬተርነት ተመዝግበው በጭነት ማጓጓዣ አገልግሎት ለተሠማሩ በዚህ መመሪያ በተዘጋጀው የደረጃ መሥፈርት መሠረት ያላቸው አደረጃጀትና የአገልግሎት ብቃት ተመዝኖ የሚሰጥ ደረጃ ነው።
4. "**የጭነት ስፔሻላይዜሽን**"ማለት አንድ ተሽከርካሪ በሚያጓጉዘው በአንድ የጭነት ዓይነት ሆኖ የዕቃው ልዩ ባሕርይ መሠረት የተወሰኑለትን ተጨማሪ ቴክኒካዊ መስፈርቶች አሟልቶ የሚሰጠው የጭነት ማጓጓዝ አገልግሎት ነው።
5 "**ዕቃ**"ማለት በየብስ የዕቃ ማጓጓዣ ሥራን ለመደንገግ ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 547/99 የተሰጠው ትርጉም ሲሆን የቁም እንስሳትን ጨምሮ ኮንቴነሮችንና ሌሎች ዕቃዎችን በዕቃ ላኪው ወይም ከዕቃ አስረካቢ በጥቅል መልክ ለጭነት የሚቀርብ ማንኛውም ንብረት ነው።
6 "**ኦፕሬተር**" ማለት የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በዚህ ደረጃ መስፈርት መሰረት በዘርፉ ተመዝግቦ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው የጭነት ትራንስፖርት ድርጅት ወይም የጭነት ትራንስፖርት ባለንብረቶች ማህበር ነው።
7. "**ማኅበር**" ማለት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ የጭነት ትራንስፖርት ባለንብረቶች ወይም ድርጅቶች የሚያቋቁሙት ማኅበር ነው።



ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

8. **"ድርጅት"** ማለት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰዱ የጭነት ትራንስፖርት የአክስዮን ማህበር፣ የግል ትራንስፖርትና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወይም ኩባንያ የሚያቋቁሙት ድርጅት ነዉ።
9. **"ድንበር ተሻጋሪ"** ማለት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወስደዉ በአገር ዉስጥና በአጎራባች ሀገሮች የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ኦፕሬተር ማለት ነው።
10. **"ተባባሪ"** ማለት ተሽከርካዉን በየትኛዉም ማህበር ሳያስመዘግብ በደረጃ ፈቃድ ከወሰዱ ድርጅቶች ጋር በሚመጥነዉ ደረጃ በተባባሪነት የሚሰራ ማንኛዉም ባለንብረት ወይም ድርጅት ነዉ።

## 4. <u>ዓላማ</u>

በድንበር ተሻጋሪ ጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ የተሠማሩ ድርጅቶችና ማኅበራት የሥራ ብቃታቸውንና የአደረጃጀት ጥንካሬአቸውን መሠረት ያደረገ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል።

1. አዳዲስ ባለሃብቶች ወደ ዘርፉ የሚገቡበትን ሁኔታ በማመቻቸት ቀጣይነቱን ማረጋገጥ፤
2. ግልፅና የጠራ የአደረጃጀት ሥርዓት በመዘርጋት በቴክኖሎጂ ውጤቶች የታገዘ ጠንካራና ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የሚከተሉ የጭነት ትራንስፖርት ድርጅቶች ፣ ኩባንያዎችና ማህበራትን ማፍራት፤
3. የጭነት ስፔሻላይዜሽንን በማበረታታት ትራንስፖርተሮች በተለያየ የጭነት ዘርፍ ዓይነት ተሰማርተው እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
4. በዘርፉ ተመሳሳይ አቅምና ብቃት ያላቸውን ትራንስፖርተሮች በመፍጠር በመካከላቸው ያለውን ውድድር ከፍ ማድርግና የተቀናጀ የሎጂስቲክስና የጭነት ትራስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት የምርቶቻችንን የገበያ ላይ ተወዳደሪነት ብቃት ማሻሻል ነው።
5. የጭነት ትራንስፖርት ዘርፉ የዉድድር ስርዓትን የሚከተል፤ጊዜና ወጪ ቆጣቢ የጭነት ማጓጓዣ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ

## 5. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ የደረጃ መሥፈርት በድንበር ተሻጋሪ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የንግድ ሥራ መስክ ተመዝግበው አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ማለትም የንግድ አክሲዮን ማህበራት፣ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበራት፣ የግል ትራንስፖርት ድርጅቶች እና በባለስልጣኑ መስሪያቤት በሚደራጁ የትራንስፖርት ማኅበራት ሁሉ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።



ነጋሽ ገ/ማርያም

# ክፍል ሁለት

## የድንበር ተሻጋሪ ደረቅ ጭነት ትራንስፖርት የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፣ ግዴታና መብቶች

### 6. የድንበር ተሻጋሪ የኦፐሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ስለመውሰድ

1. በንግድ የመንገድ የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት መሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ማህበር ወይም ድርጅት ከ200 ኩንታል በላይ የመጫን አቅም ያላቸውን ባለተሳቢ ተሽከርካሪዎችን ተሽከርካሪዎችን በመያዝ ከፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሊወስድ ይችላል።
2. በዘርፉ የተሰማሩ ወይም የሚሠማሩ ሠራተኞች የባለስልጣኑ መስሪያቤት ያዘጋጀውን አስፈላጊውን ሥልጠና ይወስዳሉ።

### 7. በማኅበር አገልግሎት ስለ መስጠት

1. የማህበራት የሥራ ዓላማ

   የሕዝብ የንግድ የትራንስፖርት ማህበሮች የሥራ ዓላማ በተቅላላዉ የማህበረተኞች ጥቅም የሚስፋፋበትንና፤

   ሀ. ለጋራ ጥቅም የሚያገለግሉትን ድርጅቶች፣ ለምሳሌ የመንገድ ጣቢያዎችን፣ የጭነት ማከፋፈያ ጽ/ቤቶችንና ጋራዦችን ማቋቋምና ማካሄድ፤

   ለ. ለማህበረተኞች ሥራ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎችና አስፈላጊ ነገሮች፣ ለምሳሌ ነዳጅ፣ ጎማና መለዋወጫ ዕቃዎችን በፊጅት ዋጋ ማቅረብና፤

   ሐ. ማህበረተኞች በየበኩላቸዉ ስለንግድ የመንገድ ትራንስፖርት የወጡትን ሕጎች ሁሉ እንዲያከብሩና እንዲተገብሩ ማድረግ ነዉ።

2. አደረጃጀት

   ሀ.. በአዋጅ 468/97 ክፍል 3 አንቀጽ 13/1 መሠረት በማኅበር በመደራጀት የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ የትራንስፖርት ማህበራት በደረጃ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት ወይም በልዩ አገልግሎት የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት ውስጥ አንዱን ብቻ መርጠው መደራጀት ይችላሉ። አገልግሎት የሚሰጡትም በተደራጁበት ደረጃና በዚያው ውስጥ ብቻ ይሆናል።

   ለ. በአንቀጽ 7 ቁጥር 2.ሀ በተጠቀሰው መሠረት በማኅበር የሚታቀፉ የተሽከርካሪዎች ብዛት በክፍል ሦስት አንቀፅ 15 መሠረት ይፈጸማል።

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

ሐ. የማህበሩ አባላት ብዛት ከ5 (አምስት) ማነስ የለበትም።

መ. በማኅበር ተደራጅተው የጭነት ትራንስፖርት ማመላለሻ አገልግሎት የሚሰጡ ኦፕሬተሮች በአዋጅ 468/97 አንቀጽ 15 መሠረት በህግ የተሰጣቸውን መብት እና ግዴታ ተፈጻሚ ለማድረግ በአደራጁ አካል በጸደቀውን የሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ይሆናል።

## 8. በግል ወይም በድርጅት አገልግሎት ስለመስጠት፣

1. በማህበር ወይም በድርጅት የጭነት ትራንስፖርት ማመላለሻ አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ ኦፕሬተሮች በደረጃ አንድ፣ሁለት ፣ሶስት፣አራት ወይም በልዩ አገልግሎት ተሽከርካሪዎችን በማቅረብ የጭነት የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ማካሄድና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ።

## 9. በተባባሪነት አገልግሎት ስለመስጠት እና ስለመመዝገብ፣

1 . ማንኛውም በጭነት ትንስፖርት አገልግሎት የተሰማራ ማህበርና ድርጅት በክፍል ሶስት የተቀመጡትን የደረጃ መስፈርት ማሟላት ካልቻለ ወይም በተቋቋሙ ማህበራት ውስጥ መመዝገብ ካልፈለገ የደረጃ መስፈርት አሟልተው የብቃት ማረጋገጫ በወሰዱ ድርጅቶች ውስጥ ተሽከርካሪዉ በሚመጥነው ደረጃ በግልጽ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ በተባባሪነት ተመዝግበዉ አገልግሎት ይሰጣሉ።

2. ከአንድ በላይ ተሽከርካሪ ኖሮት በተባባሪነት የሚመዝገብ ድርጅት አብዛኛዉ ተሽከርካሪ በሚመጥነዉ ደረጃ መሰረት በአንድ የድምበር ተሻጋሪ ፈቃድ ከወሰደ አፕሬተር ውስጥ ሊመዘገብ ይችላል።

3. በተባባሪነት የሚመዘገቡ የግል ትራንስፖርት ድርጅቶች እና ባለንብረቶች ለመመዝገብ የሚያበቃቸውን ማረጋገጫ ከባለስልጣኑ መስሪያቤት መውሰድ ይኖርባቸዋል።

4. በተባባሪነት የሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎች በሙሉ በጭነት ትራንስፖርት የንግድ ስራ ብቻ የተመዘገበ መሆን አለበት።

5. በተባባሪነት የተመዘገበ ከተባባሪነቱ ቦታ ሲለቅ ኦፕሬተሩ ለባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ማሳወቅ አለበት።

6. በተባባሪነት ለመመዝገብ የሚፈልግ ድርጅት ወደሚፈልገዉ ድርጅት ለመመዝገብ በቅድሚያ ከባለስልጣን መስሪያቤቱ ፈቃድ መዉሰድ አለበት።

## 10. በተባባሪነት ተመዝግበዉ አገልግሎት የሚሰጡ ባለንብረቶች መብት

በተባባሪነት ተመዝግበዉ አገልግሎት የሚሰጡ ባለንብረቶች የሚከተሉት መብቶች ይኖራቸዋል፤

1. በትራንስፖርት ድርጅቱ የተሽከርካሪ ማደሻና መጠገኛ ጋራዦች፤ የዕቃ መጋዘኖችና በመሳሰሉት ለድርጅቱ ተገቢዉን ዋጋ በመክፈል መገልገል፤
2. በትራንስፖርት ድርጅቱ የመለዋወጫ ዕቃ መደብሮችና የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎች ዕቃዎችና ነዳጅ ለመግዛት፤
3. ድርጅቱ ለራሱ ተሽከርካዎች የመድን ሥርዓት ያቋቋመ እንደሆነ ተገቢዉን ዋጋ በመክፈል በዚህ ስርዓት መጠቀም፤
4. የሚያገኘዉን ገቢ ለማወቅ ድርጅ የሚገለገልባቸዉን የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች፣ የሂሳብ መዝግብትና ሰነዶች በማናቸዉም ጊዜ ለመመርመር፣ ከድርሻ ሂሳብም ለሥራዉ የሚያስፈልገዉን ገንዘብ በማናቸዉም ጊዜ ለመቀበል፤
5. ተሽከርካሪዎቹን በማናቸዉም ችሎታ ባለዉ ጋራዥ ለማሰራት፤

## 11. በተባባሪነት ተመዝግበዉ አገልግሎት የሚሰጡ ባለንብረቶች ግዴታ

በተባባሪነት ተመዝግበዉ አገልግሎት የሚሰጡ ባለንብረቶች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖራቸዋል፤

1. ወጪዉን ራሱን ችሎ በተሽከርካሪዉ ላይ የድርጅቱን አርማ /ምልክት/፣ የጎን ቁጥርና ቀለም ማድረግ ወይም መቀባት፤
2. ድርጅቱ በሚያወጣዉ የጉዞ ተራ ድልድልና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተሽከርካሪዉን ማሰማራት፣ ተሽከርካሪዉ ለመሰማራት የማይችል ከሆነ ከሃያ አራት /24/ ሰዓት በፊት ወይም በተቻለ ፍጥነት በአቅራቢዉ ለሚገኘዉ የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ማስታወቅ፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተዉን ባለመፈጸም ምክንያት በጭነት ላይ ለሚደርሰዉ የአገልግሎት ዕጥረትና መጉላላት በኃላፊነት የመጠየቅ፤
4. ተሽከርካሪዉ በማናቸዉም ጊዜ የቴክኒክ አቋሙና ጽዳቱ የተሟላ እንዲሆን ማድረግ፤
5. የራሱ የሆኑት ሠራተኞች አስፈላጊዉን ትህትና እንዲሳዩና የሚጫነዉንም ዕቃ በሚገባ ተንከባክበዉ በተረከቡበት ሁኔታ ወደተፈላጊዉ ቦታ እንዲያደርሱ ማድረግ፤
6. ሌሎች የድርጅቱ ወይም የተባባሪዎቹ ተሽከርካሪዎች ሲሰናከሉ ጥሪ በሚደረግለት ጊዜ መጎተት፣ ጭነታቸዉን ወደሚፈለገዉ ቦታ ማድረስ፤
7. ድርጅቱ የሚሰጠዉን የወር የወጪ መቆጣጠሪያ ካርድ መያዝና በየወሩም መጨረሻ ይህንኑ ካርድ መልሶ ማስረከብ፤



ካሣሁን ኃ/ማርያም
ም/ ዳይሬክተር

8. ድርጅቱ በየመስመሩ ከሚመድብለት ተቆጣጣሪዎች ጋር በትብብር መስራት፤
9. በየወሩ ገቢና ወጪ ከድርጅቱ ጋር ተሳስቦ መዝጋት፤
10. ተሽከርካሪዉ አስፈላጊዉ ጥገና ወይም እድሳት እንዲደረግለት ድርጅቱ ሲጠይቅ ይህንኑ መፈጸም፤
11. ድርጅቱ የሚሰጣቸዉን የመታወቂያ ወረቀት ሁልጊዜ ይዞ መገኘት፤
12. ድርጅቱ የሚያወጣቸዉን የስራ መመሪያዎች ማክበር፤
13. በተባባሪነት የተመዘገበ ከተባባሪነቱ ቦታ ሲለቅ ለባለስልጣኑ መስሪያቤት ማሳወቅ አለበት።

## 12. ተባባሪዎችን የሚቀበሉ የጭነት ትራንስፖርት ድርጅቶች መብቶች

ተባባሪዎችን የሚቀበል የትራንስፖርት ድርጅት የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል።

1. የተባባሪዎችንና የራሱንም ተሽከርካሪዎች በተራ እየደለደለ ለማሰራት
2. ለተመደበበት አገልግሎት ብቁ ያልሆነዉን ተሽከርካሪ ብቁነቱ እንዲሟላ ለባለንብረቱ መግለጽና ብቁ እስኪሆን ድረስ ስምሪት አለመስጠት፤
3. ማንኛዉም የተባባሪ ተሽከርካሪ ለእድሳት፣ ለጥገና ወይም ለዕጥበት የሚቆምበት ጊዜ እንዲሁም አጫጫን እና አሰራር በድርጅቱ የአሰራር መመሪያ መሰረት ሊፈጸም ይችላል።

## 13. ተባባሪዎችን የሚቀበሉ የጭነት ትራንስፖርት የድርጅቶች ግዴታዎች

ተባባሪዎችን የሚቀበል የትራንስፖርት ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል።

1. እያንዳዱ ተባባሪ ከድርጅቱ ዘንድ ያለዉን የገቢና የወጪ ሂሳብ በትክክልና በተገቢዉ ሁኔታ መያዝ፤
2. ተባባሪዉ በማናቸዉም ጊዜ ሂሳቡን እንዲመረምርና ወጪም ማድረግ እንዲችል ማድረግ፡
3. በመንገድ ላይ ብልሽት የገጠማቸዉ ተባባሪ ተሽከርካሪዎችን በመኪተት ጋራዥ መውሰድ፣ ጭነታቸዉን ወደሚፈለገዉ ቦታ ማድረስ፤
4. ከላይ በተገለጸዉ መሰረት ለተፈጸመ አገልግሎት ማናቸዉንም ወጪ በሂሳቡ ማካተት፤
5. የሚያሰማራቸዉን ተሽከርካዎች የሚነዱ ሰዎች ሁሉ ተገቢዉን የማሽከርከሪያ ፈቃድ ያላቸዉ መሆኑን ማረጋገጥ እና በቂ ስልጠና በየዓመቱ መስጠት፤
6. በስምሪት /በጭነት ድልድልና በተራ አከባበር በኩል በራሱና በተባባሪ ተሽከርካሪዎች መካከል ልዩነት አለማድረግ።

# ክፍል ሦስት

## 14. የኦፕሬተርነት ፈቃድ ዓይነቶች እና የአደረጃጀት መሥፈርቶች

በሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሠማሩ ባለሃብቶች እና ድርጅቶች ለደረቅ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት እንደሚያቀርቧቸው ተሽከርካሪዎች ሁኔታ እና እንደሚመርጡት የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነት የተለያየ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣቸዋል። በዚህም መሠረት በዚህ መመሪያ በተዘጋጀው መሥፈርት የተለዩ ደረጃዎችን መሠረት አድርጎ አምስት (5) ዓይነት የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል። እነሱም፡

1. ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ 1 - ሀ እና ለ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ
2. ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ 2 - ሀ እና ለ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ
3. ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ 3 - ሀ እና ለ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ
4. ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ 4 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ
5. ልዩ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫፈቃድ ናቸው።

## 15. በድንበር ተሻገር የጭነት የትራንስፖርት ኦፕሬተር በየደረጃው መሟላት ያለባቸው ዓብይ የደረጃ መለያ መስፈርቶች

### 1. ድተ/ደረጃ 1 - ሀ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

ሀ. የሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ 0 እስከ 10 ዓመት

ለ. የአባል ተሽከርካሪዎች የመጫን አቅም ከ30 እስከ 40 ቶን

ሐ. የመነሻ የተሽከርካሪብዛት 125

መ. ቢያንስ በተለያዩ 3 ቦታዎችቅርንጫፍጽ/ቤቶችን የከፈተ

ሠ. የሰው ኃይል፣የትምህርት ደረጃ፣ ዓይነትና የአገልግሎት ዘመን በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ በዚህ ደረጃ የሚከተሉት መሟላት አለበት

1. የኦፕሬሽን ሥምሪት ክትትል አፈፃፀም ባለሙያ ብዛት ቢያንስ 5
2. የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫና የፍሊት ማኔጅመንት ክትትል ኤክስፐርት /ባለሙያ/ ብዛት ቢያንስ 3
3. የቢሮ ፀሃፊ፡ ከኮሌጅ ዲፕሎማ በቴክኒክና ሙያ፣ በጽሕፈት አገልግሎት ቢሮ አስተዳ. ብዛት ቢያንስ 3

ኳማሁን ዐ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

2. **ድት/ደረጃ 1 - ለ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት**

ሀ. የሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ 0 እስከ 10 ዓመት

ለ. የአባል ተሽከርካሪዎች የመጫን አቅም ከ20 እስከ 29.9 ቶን

ሐ. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 125

መ. ቢያንስ በተለያዩ 3 ቦታዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የከፈተ

ሠ. የሰው ኃይል፣የትምህርት ደረጃ፣ ዓይነትና የአገልግሎት ዘመን በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ በዚህ ደረጃ የሚከተሉት መሟላት አለበት

1. የኦፕሬሽን ሥምሪት ክትትል አፈፃፀም ባለሙያ ብዛት ቢያንስ 5
2. የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫና የፍሊት ማኔጅመንት ክትትል ኤክስፐርት /ባለሙያ/ ብዛት ቢያንስ 3
3. የቢሮ ፀሃፊ፡ ከኮሌጅ ዲፕሎማ በቴክኒክና ሙያ፣ በጽሕፈት አገልግሎት ቢሮ አስተዳ. ብዛት ቢያንስ 3

3. **ድት/ደረጃ 2 - ሀ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት**

ሀ. የሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ 10.1 እስከ 20 ዓመት

ለ. የአባል ተሽከርካሪዎች የመጫን አቅም ከ30 እስከ 40 ቶን

ሐ. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 100

መ. ቢያንስ በተለያዩ 2 ቦታዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የከፈተ

ሠ. የሰው ኃይል፣የትምህርት ደረጃ፣ ዓይነትና የአገልግሎት ዘመን በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ በዚህ ደረጃ የሚከተሉት መሟላት አለበት

1. የኦፕሬሽን ሥምሪት ክትትል አፈፃፀም ባለሙያ ብዛት ቢያንስ 4
2. የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫና የፍሊት ማኔጅመንት ክትትል ኤክስፐርት /ባለሙያ/ ብዛት ቢያንስ 2
3. የቢሮ ፀሃፊ፡ ከኮሌጅ ዲፕሎማ በቴክኒክና ሙያ፣ በጽሕፈት አገልግሎት ቢሮ አስተዳ. ብዛት ቢያንስ 2

4. **ድት/ደረጃ 2 - ለ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት**

ሀ. የሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ 10.1 እስከ 20 ዓመት

ለ. የአባል ተሽከርካሪዎች የመጫን አቅም ከ20 እስከ 29.9 ቶን

ሐ. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 100

መ. ቢያንስ በተለያዩ 2 ቦታዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የከፈተ

ሠ. የሰው ኃይል፣የትምህርት ደረጃ፣ ዓይነትና የአገልግሎት ዘመን በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ በዚህ ደረጃ የሚከተሉት መሟላት አለበት

1. የኦፕሬሽን ሥምሪት ክትትል አፈፃፀም ባለሙያ ብዛት ቢያንስ 4
2. የመንገድ ደህንነተ ግንዛቤ ማስጨበጫና የፍሊት ማኔጅመንት ክትትል ኤክስፐርት /ባለሙያ/ ብዛት ቢያንስ 2
3. የቢሮ ፀሃፊ፡ ከኮሌጅ ዲፕሎማ በቴክኒክና ሙያ፣ በጽሕፈት አገልግሎት ቢሮ አስተዳ. ብዛት ቢያንስ 2

5. **<u>ድተ/ደረጃ 3 - ሀ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>**

ሀ. የሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ20 ዓመት በላይ

ለ. የአባል ተሽከርካሪዎች የመጫን አቅም ከ30 እስከ 40 ቶን

ሐ. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 75

መ. ቢያንስ በተለየ1ቦታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የከፈተ

ሠ. የሰው ኃይል፣የትምህርት ደረጃ፣ ዓይነትና የአገልግሎት ዘመን በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ በዚህ ደረጃ የሚከተሉት መሟላት አለበት

1. የኦፕሬሽን ሥምሪት ክትትል አፈፃፀም ባለሙያ ብዛት ቢያንስ 3
2. የመንገድ ደህንነተ ግንዛቤ ማስጨበጫና የፍሊት ማኔጅመንት ክትትል ኤክስፐርት /ባለሙያ/ ብዛት ቢያንስ 1
3. የቢሮ ፀሃፊ፡ ከኮሌጅ ዲፕሎማ በቴክኒክና ሙያ፣ በጽሕፈት አገልግሎት ቢሮ አስተዳ. ብዛት ቢያንስ 2

6. **<u>ድተ/ደረጃ 3 - ለ ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>**

ሀ. የሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ20 ዓመት በላይ

ለ. የአባል ተሽከርካሪዎች የመጫን አቅም ከ20 እስከ 29.9 ቶን

ሐ. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 75

መ. ቢያንስ በተለየ1ቦታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የከፈተ

ሠ. የሰው ኃይል፣የትምህርት ደረጃ፣ ዓይነትና የአገልግሎት ዘመን በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ በዚህ ደረጃ የሚከተሉት መሟላት አለበት

1. የኦፕሬሽን ሥምሪት ክትትል አፈፃፀም ባለሙያ ብዛት ቢያንስ 3



ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

2. የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫና የፍሊት ማኔጅመንት ክትትል ኤክስፐርት /ባለሙያ/ ብዛት ቢያንስ 1
3. የቢሮ ፀሃፊ፡ ከኮሌጅ ዲፕሎማ በቴክኒክና ሙያ፣ በጽሕፈት አገልግሎት ቢሮ አስተዳ. ብዛት ቢያንስ 2

7. **<u>ድት/ደረጃ 4 ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት (ለድርጅቶች ብቻ)</u>**

ሀ. የአባል ተሽከርካሪዎች የመጫን አቅም ከ20 እስከ 40 ቶን

ለ. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 50

ሐ. ቢያንስ በተለየ 1 ቦታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የከፈተ

መ. የሰው ኃይል፣የትምህርት ደረጃ፣ ዓይነትና የአገልግሎት ዘመን በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ በዚህ ደረጃ የሚከተሉት መሟላት አለበት

1. የኦፕሬሽን ሥምሪት ክትትል አፈፃፀም ባለሙያ ብዛት ቢያንስ 3
2. የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫና የፍሊት ማኔጅመንት ክትትል ኤክስፐርት /ባለሙያ/ ብዛት ቢያንስ 1
3. የቢሮ ፀሃፊ፡ ከኮሌጅ ዲፕሎማ በቴክኒክና ሙያ፣ በጽሕፈት አገልግሎት ቢሮ አስተዳ. ብዛት ቢያንስ 2

8. **<u>ድት/ ልዩ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>**

**<u>ሀ. ድት/ ልዩ ገልባጭ - ሀ</u>**

1. ለግንባታ ስራ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ጭነቶችን በማጓጓዝ ስራ ላይ የሚሰማሩ ከ20 ሜትር ኩብ በላይ የመጫን አቅም ያላቸው ገልባጭ ተሽከርካሪዎች፣
2. የሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ 0 እስከ 15 ዓመት
3. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 50

**ለ. ድት/ ልዩ ገልባጭ - ለ**

1. የሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ 15.1 ዓመት በላይ
2. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 50

**ሐ. ድት/ ሎውቤድ - ሀ**

1. ግዙፍ የሆኑ ጭነቶችን በማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጡ ሎውቤድ ተሽከርካሪዎች፣



ካሣሁን ኃ/ማርያም

2. የሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ 0 እስከ 15 ዓመት
3. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 50

**መ. ድት/ሎውቤድ - ለ**

1. የግዙፍ የሆኑ ጭነቶችን በማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጡ ሎውቤድ ተሽከርካሪዎች፣
2. ሁሉም ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ዘመን ከ 15.1 ዓመት በላይ
3. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 50

9. **<u>የልዩ አገልግሎት አደረጃጀት (ስፔሻላይዜሽን)</u>**

ሀ. አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የሥጋ ምርቶችን ማጓጓዝአገልግሎት ላይ ብቻ የሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች የሚደራጁበት፣

ለ. የቁም እንስሳትን በማጓጓዝ አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች፣

ሐ. የአነስተኛ ተሽከርካሪዎችን በመጫን የማጓጓዝ አገልግሎት ላይየሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች (Car carrier)፤

መ. ጭነትን በማጓጓዝ ሥራ ለይ ድጋፍ የሚሰጡ ክብደት በማንሳት ፣ በመጫንና በማውረድ ስራ ላይ የሚሰማሩ ክሬይኖች/crane/

የሚሰጡትን የአገልግሎት ስፔሻላይዜሽንን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ተለይተው ይመዘገባሉ።

16. **<u>በሁሉም ደረጃ በእኩል መሟላት ያለባቸው የደረጃ መስፈርቶች</u>**

1. **አጠቃላይ ሁኔታ**

ሀ. ለወደብ አገልግሎት 100% ፍሊት ማኔጅመንት መሣሪያ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች ያሉት፣

ለ. በተሽከርካሪዉ ግራ እና ቀኝ የተሽከርካሪዉን ነጠላ እና ጠቅላላ ክብደት የተገለጸ፤

ሐ. በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተረጋገጠ በቂ ሠራተኞች ወይም ወኪል በወደብ ያሉት፣

መ. የራሱ የተሽከርካሪ ጥገና ጋራዥ ያለው አልያም ከታወቀ የጥገና ተቋም ጋር በውልና ማስረጃ የፀደቀ ውል ማቅረብ የሚችል።ማህበር ከሆነ አባላትንበመወከል ማህበሩ ማስረጃ አ[illegible]

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

**2. ሰው ኃይል፣ የትምህርት ደረጃ፣ ዓይነትና የአገልግሎት ዘመን**

ሀ. ሥራ አስኪያጅ፡- ማኔጅመንት፣ ኢኮኖሚክስ፣ ትራን.ማኔጅመንት /ተመሳሳይ/ BA ዲግሪናበላይ፣በሥራውበቂልምድያለው ብዛት 1

ለ. የኦፕሬሽን ስራ አስኪያጅ፡-BAዲግሪ/ዲፕሎማ በማኔጅመነት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በትራን.ማኔጅመንት በጂኦግራፊ/ተመሳሳይ/ ብዛት 1

ሐ. የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ፡-BA ዲግሪ ወይም ዲፕሎማበማኔጅመንት፣ ኢኮኖሚክስ/ ተመሣሣይ ብዛት ቢያንስ 1

መ. የኦፕሬሽን ሥምሪት ክትትል አፈፃፀም ባለሙያ፡-ዲግሪ /ዲፕሎማ/ ትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ ጂኦግራፊ ብዛት ቢያንስ 1

ሠ. የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫና የፍሊት ማኔጅመንት ክትትል ኤክሰፐርት/ባለሙያ/፡- ዲግሪ/ዲፕሎማ፣ 10+2 በትራፊክማኔጅ፣ በሶሻልሣይንስ/ተመሣሣይ/፣ በጂኦግራፊ IT \ብዛት ቢያንስ 1

ረ. ፀሐፊዎች፡ ከኮሌጅ ዲፕሎማ በቴክኒክና ሙያ፣ በጽሕፈት አገልግሎት ቢሮ አስተዳ. ብዛት ቢያንስ 1

ሰ. በአገር ውስጥ ላሉ በየቅ/ጽ/ቤቱ የሚሠሩ እንደ ሥራው ደረጃ የተሟላ የሰው ሀይል ዝርዝር ይቀርባል።

**3. የመገልገያ ዕቃዎች/መሣሪያዎች/**

ሀ. መረጃ ለመያዝና ለመለዋወጥ አጋዥ በሆኑ መሳሪያዎች በደንብ የተደራጀ ቢሮ ያለውና አድራሻውን በግልፅ የሚያሳውቅ፣

ለ. የኢንተርኔት አገልግሎት እና የራሱ ድረ-ገጽ ያለው፣

ሐ. ስልክ ቀጥታ መስመር፣ ሞባይል ስልክ ወይም ዘመናዊ የመገናኛ መስመር

መ. የመስክ ተሽከርካሪ (4 ዊል ድራይቭ)።

**4. መሟላት ያለበት ሕትመት**

ሀ. የራስጌና የግርጌ ማህተም፣

ለ. የተሽከርካሪ ጭነት ማዘዣ ሰነድ /FO/፣

ሐ. የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ መከታተያና መቆጣጠሪያ /Log Book/፣

መ. የገንዘብ መቀበያና የወጪ ማዘዣ ሰነዶች፣

ሠ. የባለስልጣኑ መስሪያቤት በሚያወጣዉ ስታንዳርድ መሰረት የማህበሩን ወይም የድርጅቱን ስም እና አርማ የያዘ የጐን ስቲከር Sample፣

ረ. ማህበር ከሆነ የባለስልጣኑ መስሪያቤት ባወጣዉ ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተዘጋጀና በአባላቱ የፀደቀ ደንብ፣

ሰ. ሌሎች ለስራ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ካሉ ኮፒው ይቀርባል።

## 17. የደረጃ ማሻሻያ እና ክለሳ

1. በመስፈርቱ መሠረት ደረጃ የተሰጠው ተቋም በባለስልጣኑ መስሪያቤት ፈቃዱ ሲታደስ በየዓመቱ እየተገመገመ እንዲሁም የደረጃ ማሻሻያ ጥያቄ ሲያቀርብ ወይም በክትትል ሲገኝ ደረጃውተመዝኖ ከፍ ወይም ዝቅ እንዲል ይደረጋል።
2. በዚህ መስፈርት የተቀመጡትን ነጥቦች በማናቸውም ጊዜ አሻሽሎ ወይም አጎድሎ ከተገኘ ሊለወጥ ይችላል።

# ክፍል አምስት

## 18. የፈቃድ ጥያቄ አቀራረብና አፈፃፀም

ማንኛውም የፈቃድ አገልግሎት ጠያቂ ጥያቄውን የሚቀርበው በመስፈርቱ መሠረት የሚያሟላውን ደረጃ በመለየት ነው። ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሰነዶች አያይዞ ያቀርባል:-

1. የትራንስፖርት ማህበራት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 ከቁጥር 1 እስከ 6 ከደረጃ አንድ እስከ ሶስት ከተቀመጠዉ መስፈርት የተቀመጠዉን የተሽከርካሪ ቁጥር 100% (በመቶ) ተሟልቶ መገኘት አለበት።
2. የትራንስፖርት ኩባንያዎች፣ አክሲዮን ማህበራት፤ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበራት እና የግል ትራንስፖርት ድርጅቶች ከአንድ (1) እስከ ሶስተኛ (3ኛ) ደረጃ የተቀመጠዉን የተሽከርካሪዎች ቁጥር 80% (በመቶ) አሟልተው ከተገኙ ደረጃዉን እንዳሟሉ ይቆጠራል።
3. ሥራው የሚከናወንበት ቦታ ቋሚ ቢሮ ስለመዘጋጀቱና ቢሮው የግል ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ /ኮፒ/ የኪራይ ከሆነ ቢያንስ የአንድ ዓመት በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ ሕጋዊ የኪራይ ውል ማስረጃ ከኮፒው ጋር፤
4. የሰው ኃይል ዝርዝርና የሕትመት ናሙና ሰነድ ከኦሪጅናሉ ከኮፒ ጋር፤
5. የሰው ሀይል፣ የተሽከርካሪ ዝርዝር፣ የመገልገያ መሣሪያዎችና ሌሎችንም መረጃዎች በሚሰጠው ፎርማት መሠረት ሞልቶና አረጋግጦ ያቀርባል፣
6. በመሥፈርቱ የተዘረዘሩት ግዴታዎች፣ የቢሮ አደረጃጀትና የመገልገያ መሳሪያዎች በሠነድ መሟላታቸው የሚያረጋግጥ በፈቃድ ጠያቂዉ ፊርማና ማህተም የተረጋገጠ ሰነድ ሲቀርብ ለአገልግሎት ጠያቂው ተቋም ወቅታዊ የደረጃ ምደባ ማስረጃ ይሰጣል።

ተገኘወርቅ ኃ/ማርያም
ምክትል ዳይሬክተር

7. ማንኛውም ደረጃ የተሰጠው ትራንስፖርት ድርጅት፣ ማህበር የሙያ ሥነ-ምግባር አክብሮ ለማገልገል ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ቅጽ መሠረት ፈቃድ ጠያቂው አንብቦ የፈረመበት ሠነድ፣ የደረጃ ምደባ ማስረጃው የሚያገለግለው ለአንድ (1) ዓመት ነው።

## 19. የምዝገባ ዕድሳት

1. ለባለንብረቶች ማህበራት ፈቃድ ዕድሳት ከመስከረም 1 እስከ የካቲት 30
2. የድርጅቶች ፈቃድ ዕድሳት ከሐምሌ 1 እስከ የካቲት 30
3. መስፈርቱን አሟልተው ደረጃ የወሰዱ ኦፕሬተሮች በእድሳት ወቅት በመስፈርቱ የተቀመጠውን የእድሜ ወሰን 90 በመቶ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች አሟልተው መገኘት አለባቸው።
4. በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው የዕድሜ ወሰን የሚያገለግለዉ ለ2-ዓመት ብቻ ይሆናል።

## 20. የአገልግሎት ክፍያ

መሥፈርቱን አሟልተው ደረጃ እና የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጣቸው የጭነት ትራንስፖርት ኩባንያዎች፣ ማኀበራት የግል ትራንስፖርተሮች እና ባለንብረቶች በመንግሥት የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላሉ።

## 21. የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ኦፕሬተሮች መብት እና ግዴታ

1. የተሟላ የሥራ ሬኮርድና ሠነድ አሟልቶና አደራጅቶ የመያዝ፣
2. የማህበሩ ወይም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ሲለቁ እና ሲቀጠሩ ማሳወቅ
3. የመንገድ ትራፊክ ደኅንነት ዩኒት በማቋቋም አደጋን ለመቀነስ በሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ተሣታፊ የመሆን፣
4. በባለስልጣኑ መስሪያቤት የወጡ የአሰራር ደንብ እና መመሪያዎችን የማግኘት፤
5. በባለሥልጣኑ መ/ቤት የወጡ ደንቦችና ሕጐችን አክብሮ በተሰጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መሰረት አገልግሎት የመስጠት።
6. የባለስልጣኑ መስሪያቤት በሚያዘጋጃቸው በተለያዩ የውይይት መድረኮች መሣተፍ፣
7. ያሉትን ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ የተሸፈነ ርቀት የተጓጓዘ ጭነት ብዛት የሰው ኃይልና የቢሮ አደረጃጀት ወቅታዊ የገበያ ዋጋ /ታሪፍ/ መረጃና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በየወሩ ለትራንስፖርት ባለሥልጣን የመስጠት ኃላፊነትና ግዴታ አለበት።

# ክፍል ስድስት

## 22. የሥነ-ሥርዓትና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች

የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም የሥነ-ምግባር ጉድለቶችን ስለመፈጸም ያመለክታሉ፤

1. ማንኛውም ባለንብረት፣ ድርጅት ወይም ማኅበር በዚህ መመሪያ መሠረት የጭነት የመንገድ ትራንስፖርት የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው አገልግሎት ከሰጠ፣
2. ማንኛውም ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫውን ወቅቱን ጠብቆ ካላሳደሰ፣
3. ከባለስልጣኑ መስሪያቤት የአባልነት መመዝገቢያ ደብዳቤ ሳይኖር ባለንብረቶችን ወይም ድርጅቶችን በአባልነት የመዘገበ ወይም ለተሽከርካዎች የመውጫ /የስምሪት/ ሰነድ መስጠት፣
4. ማህበሩ የሚገኝበትን አድራሻ ሲቀይር እና ስልክ ሲቀይር በአምስት (5) ቀናት ውስጥ ያላሳወቀ፤
5. የማህበሩ ወይም የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ስለቁ እና ሲቀጠሩ ለባለስልጣኑ መስሪያቤት አለ ማሳወቅ፤
6. ማህበራት በሞዴል መተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በየሁለት (2) ዓመቱ የአደራጁ አካል ተወካይ በተገኘበት ጠቅላላ ጉባዔ አለመጥራት እና በውጭ ኦዲተር ሂሳቡን አለማስመርመር፤
7. ድርጅቶች፣ የግል ትራንስፖርተሮች የአገር ውስጥ ገቢ ክሊራንስ በማቅረብ በየዓመቱ ካላሰደሱ፤
8. ማህበራት የአንድ (1) ዓመት የክንውን ሪፖርት እና የጠቅላላ ጉባኤ ቃለጉባዔ አቅርበዉ ካላሳደሱ፤
9. ማንኛውም የጭነት የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ማኅበር ወይም ድርጅት ፈቃዱን ለዕይታ በሚያመች መልኩ አስቀምጦ አለመገኘት፣ በፌደራል ወይም ክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ቢሮዎች ወይም አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅም ለማሳየት ፈቃደኛ ካልሆነ፣
10. የትራንስፖርት ማህበራት እና ድርጅቶች የስም ስያሜአቸውን በቢሮአቸው ላይ አለመለጠፍ፤
11. ማንኛውም ኦፕሬተር ፈቃድ በተሰጠበት ወቅት ተሟልተዋል በሚል በፊርማ ያረጋገጣቸው መመዘኛዎች በቁጥጥር ወቅት ተሟልተው

12. የስብሰባ ጥሪ ተደርጐለት ወይም እንዲደርሰው ተደርጐ ያለበቂ ምክንያት ካልተገኘ፣
13. እንደ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዳቸው ደረጃና ዓይነት ለሕዝብ እና ለሃገር ጥቅም ሲባልና በመንግሥት ውሣኔ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ተመድበው አገልግሎት እንዲሰጡ ሲጠየቅ ተባባሪ ሆኖ ካልተገኘ፤
14. የማኅበሩን ወይም የድርጅቱን ዓርማና ማኅተም ሙሉ አድራሻ (ስልክና ፖስታ ወዘተ...) የያዘየጭነት ማዘዣ፣ ሎግ ቡክ እናሌሎች የኦፕሬሽን ሰነዶችን አለማዘጋጀትና አለመጠቀም፣ እንዲሁም ላልተፈቀደለት ተሽከርካሪ እስቲከር እና ፍሬት ኦርደር እንዲጠቀሙ መፍቀድ፤
15. የማህበሩ የቦርድና የኦዲት እና ኢንስፔክሽን አመራሮች እንዲሁም አባላት ተሽከርካሪያቸውን ሲሸጡ ለባለስልጣኑ መስሪያቤት ያለማሳወቅ ከማህበሩ የአገልግሎት ተጠቃሚ ሆነው ሲገኙ፤

## 23. <u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

የአስተዳደር እርምጃዎች ዝርዝር አፈጻጸም በቀጣይ ይወጣል።

# <u>ክፍል ዘጠኝ</u>

# <u>አንቀጽ አሥራ አንድ</u>

## 24. <u>ስለቁጥጥር</u>

ይህ የደረጃ እና የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ሲጣስ የሚቆጣጠሩ የባለስልጣኑ የፈቃድ ክትትልና ቁጥጥር ሠራተኞች ናቸው። ይሁን እንጂ ኅብረተሰቡ የቁጥጥሩ አጋዥ ኃይል እንደመሆኑ አስተያየቶችና ጥቆማዎችን በመስጠት መሳተፍ ይችላል።

## 25. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የትራንስፖርት ድርጅቶች፣ ማኅበራትና ግለሰቦች የመተባበር ግዴታ አለባቸው።



Federal Democ... Ministry

## 26. የቁጥጥር አፈፃፀም ሂደት

1. ለቁጥጥር የተሠማራው ሠራተኛ ራሱን የሚገልጽ መታወቂያ ይዞ መገኘትና ሲጠየቅ ማሳየት አለበት፣

2. በቁጥጥር ሂደት ጥፋት ተፈጽሞ ከተገኘ ተቆጣጣሪው (የባለስልጣኑ መስሪያቤት ተወካይ) ወዲያውኑ የጥፋት ሪፖርት ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ማቅረብ አለበት።

3. በዚህ መመሪያ የተካተቱ ነገር ግን በሌላ የትራንስፖርት አዋጅ ወይም ደንብ የተሸፈኑ የቅጣት ዓይነቶች ካሉ በወጡበት አዋጅ ወይም ደንብ መሠረት በዚያው በኩል ተግባራዊ መደረግ አለባቸው።

## 27. መመሪያውን የመሻር ወይም የማሻሻል ስልጣን

ይህን መመሪያው ለማሻሻል ይሁን ለመሻር ሥልጣን ያለው የፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው።

## 28. የተሻሩ መመሪያዎች

ይህን መመሪያ የሚጻረሩ ሌሎች መመሪያዎች ሁሉ በዚህ የአገልግሎት አፈጻጸም መመሪያ ተሽረዋል።

## 29. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፡-

ይህ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የደረጃ መሥፈርት መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ካሣሁን ኃይለማርያም**
**የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**
**አዲስ አበባ**

**<u>አባሪ 1</u>**

## <u>በደረጃ መስፈርቱ መሠረት መረጃዉ ስለመሟላቱና ትክክል ስለመሆኑ</u>

## <u>የተሰጠ ማረጋገጫ</u>

እኔ/እኛ_______________ አድራሻ ___________ክ/ከተማ__________ወረዳ__ _______

ልዩ መጠሪያ____________ የቤትቁጥር_____________የስልክ ቁጥር____________

ለድርጅታችን ☐ ለማኅበራችን ☐ለደረጃ____ምድብ_____የወጣውን መሥፈርት የምናሟላ ስለሆነ ደረጃ እንዲሰጠን እንጠይቃለን። ደረጃው ቢሰጠን

1. በመሥፈርቱ መሠረት የተሸከርካሪውንም ሆነ ለተቋሙ የተሰጠውን ደረጃ በተሟላ ሁኔታ በመጠበቅ አገልግሎት እንሰጣለን።
2. በንግድ ህጉ በየብስ ዕቃ የማጓጓዝ ሥራ ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 547/99 እና የትራንስፖርት አዋጅ 468/97 ሕግና ደንብ አውቀንና ተገንዝበን ሥነ-ምግባር ያለው አገልግሎት እንሰጣለን።
3. በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚጠየቁ አስፈላጊ መረጃዎችን እንሰጣለን፣ በተቋማችን የአደረጃጀትና ሌሎች ለውጦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ለትራንስፖርት ባለሥልጣን እናሳውቃለን።
4. የሥራ አፈፃፀማችን በትራንስፖርት ባለሥልጣንና በሌሎች ገለልተኛ አካላት በየጊዜው እየተገመገመ የሚሰጠንን ደረጃ እንቀበላለን።
5. ከዚህ ደብዳቤ ጋር በአባሪነት የተያያዙት/የቀረቡት መረጃዎች ሁሉ ትክክል ስለመሆናቸዉ ከዚህ በታች ባለዉ ፊርማና ማህተም እናረጋግጣለን

ሥም፡- ______________________________

ፊርማ፡- ______________________________

ማህተም

**<u>አባሪ 2</u>**

## የተቋሙ ንብረት የሆኑ ወይም በተቋሙ የተደራጁ የጭነት ተሽከርካሪዎች ዝርዝር

**/በተቋሙ የሚሞላ/**

| የባለንብረት ስም | የመኪና የሰሌዳ ቁጥር | የሞተር ቁጥር | የመኪና ሻንሲ ቁጥር | የተሳቢ ሰሌዳ ቁጥር | የተሳቢ ሻንሲ ቁጥር | የስራት ዘመን | | የመጫን አቅም በኩንታል | | ጠቅላላ ድምር በኩንታል | የፍሊት ማኔጅመንት መሣሪያ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች ብዛት | የአገልግሎት ዓይነት | ተጨማሪ መግጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የመኪና | የተሳቢ | የመኪና | የተሳቢ | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |

*<u>ማሳሰቢያ</u>፡የአገልግሎት ዓይነት ሎቤድ፣ ሀይቤድ፣ ቁም እንስሳት ማጓጓዣ፣ በልክ ጭነት ማጓጓዣ ወዘተ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።*